CGIAR Sustainable Intensification of Mixed Farming Systems

# Financial Literacy for Smallholder Livestock Keepers

## A Training Manual

### (Amharic Version)

Muluken Zeleke[1], Jane Wamatu[1], Yehuwanis Goshu[2], Elsa Mengiste[2], Tesfa Getachew[3]

[1] International Center for Agricultural Research in the Dry Areas (ICARDA), Addis Ababa, Ethiopia

[2] Bassona Worena District, Cooperative office, Debre berhan, Ethiopia

[3] Debre Berhan Agricultural Research Center, Debre berhan, Ethiopia




**Published by: International Center for Agricultural Research in the Dry Areas (ICARDA)**

November 2022

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
Amhara National Regional State

ARARI

ICARDA
Science for resilient livelihoods in dry areas
CGIAR

The Sustainable Intensification of Mixed Farming Systems Initiative aims to provide equitable, transformative pathways for improved livelihoods of actors in mixed farming systems through sustainable intensification within target agroecologies and socio-economic settings.

Through action research and development partnerships, the Initiative will improve smallholder farmers' resilience to weather-induced shocks, provide a more stable income and significant benefits in welfare, and enhance social justice and inclusion for 13 million people by 2030.

Activities will be implemented in six focus countries globally representing diverse mixed farming systems as follows: Ghana (cereal–root crop mixed), Ethiopia (highland mixed), Malawi: (maize mixed), Bangladesh (rice mixed), Nepal (highland mixed), and Lao People's Democratic Republic (upland intensive mixed/ highland extensive mixed).

© 2022

This publication is licensed for use under the Creative Commons Attribution 4.0 International Licence - https://creativecommons.org/licenses/by/4.0.

Unless otherwise noted, you are free to share (copy and redistribute the material in any medium or format), adapt (remix, transform, and build upon the material) for any purpose, even commercially, under the following conditions:

ATTRIBUTION. The work must be attributed, but not in any way that suggests endorsement by the publisher or the author(s).

Amhara National Regional State

ICARDA Science for resilient livelihoods in dry areas

CGIAR

## Training Manual for Financial Literacy

The manual "Training for Financial Literacy" is a practical manual, appropriate for smallholder farmers to ensure that women and men, including the youth, have access to financial literacy knowledge and skills that they need to effectively manage their money for improved livelihoods

It aims to enhance a combination of awareness, knowledge, skills, attitude, and behavior required to make informed financial decisions and ultimately achieve financial well-being when engaging in sheep fattening and other livestock-related commercialization activities along livestock value chains in Ethiopia. The manual consists of various modules that can also be used individually, tailored to the respective training groups.

Amhara National Regional State

ICARDA
Science for resilient livelihoods in dry areas
CGIAR

# የሥልጠና ማኑዋል

## የገንዘብ እና ሕብረት ሥራ ማህበር አስተዳደር በበግ ድልብ ለተሰማሩ ወጣቶች እና ሴቶች የተዘጋጀ

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
Amhara National Regional State

ICARDA
Science for resilient livelihoods in dry areas

CGIAR

Contents

**1. መግቢያ ..... 6**

**1.ህብረት ስራ ትርጉም** ..... 6

**2. የኅብረት ሥራ ማህበር ዓላማዎች ..... 6**

**3. የኅብረት ሥራ ማህበራት መሠረታዊ መርሆዎች ..... 6**

**4. የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የአባላት እሴቶች ..... 7**

**5. የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሥነ-ምግባር እሴቶች፣ ..... 9**

**6. የኅብረት ሥራ ማኅበር መተዳዳሪያ ደንብ ..... 12**

**8. የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባራትና ኃላፊነቶች፣ ..... 13**

**9. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች ..... 14**

**10. የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ለመሆን መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ..... 15**

**12. የገንዘብ ቁጠባ አስፈላጊነት ..... 16**

12.1 የገንዘብ ቁጠባ ዓላማ ..... 16

12.2 የገንዘብ ቁ/ ተግባር፣ ..... 17

12.3 መደበኛ ቁጠባ፣ ..... 17

12.4 መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ፣ ..... 17

# 1. መግቢያ

## 1.1 ህብረት ስራ ትርጉም

“ኅብረት ሥራ ማኅበር ማለት በጋራ ባለቤትነት በ**ዲሞክራሲያዊ** መንገድ በሚቆጣጠሩት **ድርጅታቸዉ** አማካኝነት የጋራ **ማኅበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ፍላጐታቸዉን** ለማርካት **በፈቃደኝነት** የተገናኙበት ራስ-ገዝ የሆነ የሰዎች ስብስብ ነው**”**

“ኅብረት ሥራ ማኅበር ማለት በአባላት ከፍተኛ ተሣትፎ ተመጣጣኝ ካፒታል አውጥተው **በዲሞክራሲያዊ** ሁኔታ የሚቆጣጠሩበትና ትርፍና ኪሣራን በፍትሃዊ መንገድ በሚካፈሉበት **ድርጅታቸዉ** አማካኝነት **የጋራ ግባቸዉን** ለማሣካት **በፈቃደኝነት** የተገናኙ ሰዎች ስብስብ ነው”

# 2. የኅብረት ሥራ ማህበር ዓላማዎች

1) አባላት በተናጠል በመሥራት ሊወጧቸው የማይችሏቸውን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ችግሮችን በተባበረ ጥረት መወጣት፣ መቋቋም እና መፍታት፤

2) አባላት ያላቸውን ዕውቀት፣ ሀብትና ጉልበት በማቀናጀት የተሻለ ውጤት ማግኘት፤

3) በአባላት ዘንድ በራስ መተማመንን ማጎልበት፤

4) ለማምረት የሚያስፈልገውን ወጪና የአገልግሎት ዋጋን በመቀነስ አባላት የሚፈልጉትን ግብአት ወይም አገልግሎት በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ እና ምርታቸው ወይም አገልግሎታቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ እንዲያገኝ ማስቻል፤

5) የቴክኒክ ዕውቀትን እና የሥራ ፈጠራን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፤

6) በአባላት መካከል የቁጠባ ባህል እንዲዳብር እና እንዲስፋፋ ማድረግ፤

7) ለአባላት የብድር አገልግሎትን በመስጠት ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፤

8) ለአባላት የብድር የሕይወት መድን ዋስትና መስጠት፤

9) አባላቱ በግላቸው ቢሰሩ ኖሮ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳትና ኪሣራ በጋራ በማካፈል የእያንዳንዱ ሰው ጉዳትና ኪሣራ መቀነስ፤

10) አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አቅማቸውንና ባህላቸውን ማጎልበት፡፡

# 3. የኅብረት ሥራ ማህበራት መሠረታዊ መርሆዎች

xÆLnT bfÝdŸnTÂ bF§gÖT §Y ytmsrt XÂ lhùlùMKFT yçn#

ለ. ÄþäK‰sþÃêE xs‰RÂ xm‰R#

ሐ. የአባላት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ

መ. nÉÂ ‰SN b‰S ¥StÄdR#

ሠ. tk¬¬Y TMHRT# oL«ÂÂ mr© mS«T

ረ.  kl¤lÖC xÒ y~BrT o‰ ¥Hb‰T UR ~BrT mF«R

ሰ. lxµÆbþ ዘላቂ L¥T _rT ¥DrG#

***<u>አባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>***

- በማኅበሩ የሥራ ክልል የሚገኝ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 እና በማሸሻያ አዋጁ 402/1996 እንዲሁም በክልሉ አዋጅ 220/07በፌደራሉ 985/09 መሰረት የተመዘገበና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ መመሪያዎችን ተግባራዊ የሚያደርግ፣
- በማድለብ ላይ በተወሰነው ጊዜ ጥራቱን የጠበቀ ድልብ ማቅረብ የሚችል፣
- በማህበሩመተዳደሪያ ደንብ፣ ውስጠ ደንብና ልዩ ልዩ መመሪያዎችን የተቀበለና ለመፈፀም ፈቃደኛ የሆነ፣
- በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተወሰነውን የመመዝገቢያ ክፍያና ቢያንስ ዝቅተኛውን የዕጣ ብዛት መግዛት የሚችል፣
- በሌላ ተመሣሣይ ማኅበር አባል ያልሆነ፡፡
- እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ
- ቢያንስ ማድለብ የሚችል እና በማድለብ ንግድ ያልተሰማራ መሆን አለበት
- *በህግ መብቱ ያልተገፈፈና የአእምሮ መታወክ የሌለበት*
- ገቢ ያለው፣ በአንድ አካባቢ የሚኖር ወይም በአንድ ድርጅት ወይም መስሪያ ቤት የሚሰራ፣
- . በፋይናንስ አገልግሎት ተመሳሳይ ፍላጐትና ዓላማ ያለው፣
- . በማኅበሩ የሥራ ክልል የሚኖር ወይም የሚሠራ፣

## 4. የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የአባላት እሴቶች

ሀ) ራስን በራስ መርዳት፣

ለ) የግል ኃላፊነትን መወጣት፣

ሐ) የዲሞክራሲ ባህልን ማስፋፋት፣

መ) እኩልነት፣

ሠ) ፍትሃዊነት፣

ረ) ወንድማማችነት፣ ይሆናሉ፡፡

**<u>1.W^¿ LuG /W^¿ LY«r</u>**

- \ዎv z/RW MzlY £ሚë¦keLår ¦Ft'å¿ £µ¿šn& £µåGlr~ £˜'ådr †iN lMd~¯r lp~¼G ¼Tr Eéµ„ ŠMëvE'å lF¨ lŠÙpf ªT± £paE 'åºîr EM·,r ˆ¿ªMëvEå lML¿ ˆ~ ˆY·ºf lLD¿ }'å::
- znTr RW MzlWpýN £Më¿d]d\år £†mFr¿ £plqp} µ¿šn& ˆ'ådr~ µåGlr †d~³s 'åºîqM lD} ˆ¿i^g\î £paE 'åºîr EM·,r lM\n }'å::
- ✓ ˆ¦¿«¿«è †mG lMzlU 'å^¼ £Më¦ªYµ'å¿ ˆ¿i^g\î £EîF'å¿ †mG v·Y £MëÔq~ £paE pºgMë £Më¦ªY· LD}å¿ l¼Gdr ML¿~ ¨C¿ lMTµåN EîEøv¿ £MëT« nu Q¨D¿ W\å¿ lpaE Aå}ïq £MëT« LD}å¿ Lµ¿šn pµlé }'å::
- ✓ ŠšêC maµY †mFrN D}å MzlWr £MzlWt'å 'åºîqM}r~ £v·Zut'å LÔqr ˆY^ l^Y^ £Më¦ªYµår ¼Tr~ †ድገr ˆ¿³ ŠEîF †‹G lMëµ„ ድ¶Ù~ ˆY«q †ELD}å¿ l¼Gdr M'i ¨µmt"G

**<u>2.£W^ yFÖ}r</u>**

- ➢ ኅብረት RW MzlWr¿ ŠEîEøv ድY³sv G¤ ŠMë¦ªY¹t'å mCV¦r mElîsv፣ LV•v፣ £†µG·Eør pºgMë•v፣ 'šp. †mFr LD~t'å }'å::
- ➢ lLD}åN MzlU¿ 'åºîqM~ dG»× †µG·Eør ˆ¿«é\¼~ ቀጣይነት ˆ¿«éዋሪው ለMT·& Šv·Zv~ Š†ª¶•v £Lºli~ £L¿ŠmŠn& Š†Œ]V ˆ¿i^g\î•v £LŠFŠG yFÖ}r £†mFr }'å::
- ➢ ˆ¦¿«¿«è †mG MzlU £Më¦^Lš·l'å †lTqv ˆ¿i^g\î £W\å ¼Tr lLD}å £Mëª\p'å¿ ¦CG †mFr £MzlWt'å¿ £˜Er Š˜Er ˆ¿i^g\î l†·mlå mELŠqpFt'å~ mELNWqt" NŒ¿¦r MzlWt'å £Më¦¶¼L'å¿ v·Y £L‹ÔG~ £LÙqr yFÖ}r †Emt'å:

**<u>3.«éOŒW\é</u>**

- ✓ znTr RW MzlWr †mFr l¿gr £Mëj»º[t'å~ £MëQpÕmt" «éOŒW\é¦"ì Y³sv ~t'å::
- ✓ lLPTq"ì MzlY ªT± †¿ድ †mG †¿ድ ድNÎ lMëE'å «éOŒW\é¦"ì Î¿\ BQn F¨ £pLPTp ˆŠåG £L'\¿ Lnr †E'å::
- ✓ znTr RW MzlWr¿ £LNWr yFÖ}r¿ £'\ª ÞEé\é•v¿ lLiTÎ& 'åQ}ï•v¿ lL'\¿~ lL]\Eår Bìªsv †mFr¿& RW †^Šé¦´v¿~ EîEøv i¼Y PWp…v¿ ˆ¿ª£yFÖ}qt'å Lº¿ ˆ¿«éQpÕ~ †^p"Î‰ ˆ¿«é¦ªYµå ¦ªY¶Eå::
- ✓ lznTr RW MzlWr 'å^¼ M¿ƒ'åN 'åQ}ï l£ªT±'å †LWY EL^ºr~ 'åQ}ï EL'\¿ RG»¿ mFt'å £MzlU †‹Fr †nFÁ ድNÎ nu ¨'\~G::

**4.ˆŠåG}r**

- ❖ lM¿ƒ’åN £znTr RW MzlWr ˆ¿i^g\î E†mFr ’¨N E\’å G´v AåEå ¦EN¿N £Anr Lº¿& £šY& £H¨M•r& £ÞEpí‹ †LE‹Šr የጾታ፣ ወዘተ. N¿N —¨}r G¤}r Q¨ªT· l\’å}qt’å nu ˆŠåG Lnr~ ŒnY ˆ¿«é•ኖራt’å ¦^ÔG¶G::
- ❖ lLD}åN znTr RW MzlWr M¿ƒ’åN \’å ˆŠåG ªT±~ Lnr ¦E’å LD}å የሚT¶ገ¼mt’å LድT•ኮv ~t’å::
- ❖ ¨C LPTq”ì ·¿›lî lMzlWr †LWY †‹Fr& li¼Y PWp…ች~ ˆ¿«éAåN l˜¦¿«¿«è †mG በ¼Gdr ·¿›lî Eé¦œlr £Mëµm~ l˜Er Š˜Er ˆ¿i^g\î lrŒŒG p·mW”ì LªT· †Elr::
- ❖ l\•v ˆŠåG}r F¨ £pLPTp †µG·Eør £M¨\¼ MzlY lN¿N LGŠå šFf~ ’åºîqM EéD¿ ˆ¿ªM¨vG Eéq’i ¨µm”G::

**5.ÙrB”ì}r**

- ➢ znTr RW MzlWr lMë¦Š~’å}år M¿ƒወåN MzlW”ì~ †é••ኮኖMë¦”ì ˆ¿i^g\î ’åºîqM £MëD}år †mFr lµ¿šn፣ l˜’ådr~ lµåGlr lMë¦lTŒpýr †^p”Î‰ Lº¿ LPTr }’å::
- ➢ ^ED}N MzlWr E†mFr £MëPºår †é•ኮኖሚያዊም D} MzlW”ì ¼iN ወይም †µGµEør ˆ¦¿«¿«è †mG EMzlU mlTŠp’å †^p”Î‰ Lº¿ LPTr LD¿ †Elr::
- ➢ EMzlU nšå †^p”Î‰ ¦ªTµå nšå pºgMë EéD}å ¨µmG::
- ➢ l†¿ÑU †}^pf †^p”Î‰ ¦ªTµå †}^pf pºgMë EéD¿ ¨µmt”G::

**6.’¿ድMv}r**

- ➢ አ¦¿«¿«è \’å lpÔ¼Z ŠEîF’å £pE£ £W\å †LE‹Šr~ ÙF¸r ’¨N v·Y E•E•’å ¨vFG
- ➢ lEîF lŠåG znTr RW MzlWr ª·O £MëLPTpýr pLQQ¨ v·Y፣ —FM~ ÙF¸r mFt“ \•v }’å
- ➢ Š}šêC LPTq”ì BQov lL}]r ˆ¦¿«¿«è †mG lMzlU †LWY Bìªr፣ l†µG·Eør †\»¼~ lG¤ G¤ LድT•ኮች £Më¦ªY¶t’å ˆ¿i^g\î•v AåEå l·Eå £pE£ pºgMë ELD¿ ’¨N ·E\m”ì v·Y¿ ELÙqr~ ÙF¸r¿ EMQ‹r Q¨D¿ £†n›f’å¿ †mFr ÙF¸r~ v·Y LPTr mªTµ LGŠå p¿d]i_ pºgMë ELD¿ ¼Tr MT· †Elr

## 5. የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሥነ-ምግባር እሴቶች፣

ሀ) ታማኝነት፣

ለ) ግልፀኝነት፣

ሐ) ተጠያቂነት፣

መ) አሳታፊነት፣

ሠ) ማህበራዊ ኃላፊነት፣

ረ) ለሌሎች ማሰብ፡፡

**ስለኅብረት ሥራ ማህበራት አመሠራረት**

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደየባህሪያቸው ከመሠረታዊ እስከ ፌዴሬሽን በየደረጃው ሊመሰረቱ ይችላሉ፡፡

2) የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር፣

ሀ) በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም በሚሠሩ ወይም በተወሰነ ሙያ በተሰማሩ ግለሰቦች፣ እና

ለ) ቁጥራቸው ከሃምሣ በማያንሱ አባላት ይደራጃል፡፡

1) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ለ) ቢኖርም የሥራ ባህሪያቸውን እና የኢኮኖሚ አዋጭነታቸውን መሠረት በማድረግ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የመነሻ ቁጥሩን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡ ሆኖም የመነሻ ቁጥሩ ከ10 ሊያንስ አይችልም፡፡

4/ በፌዴራል ደረጃ የሚደራጅ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት ነዋሪነታቸው ከሁለት እና ከዚያ በላይ ከሆኑ ክልሎች የተውጣጡ ግለሰቦች መሆን አለባቸው፡፡

5/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበራትን በፌዴራል ወይም በክልል ደረጃ በማደራጀት የሚመዘግብ ይሆናል፡፡

*የማህበሩ የኮሚቴ አባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎች*

የሚከተሉትን የማያሟላ ¾ማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ አባል፣ ሥራ አመራር ኮሚቴ አባል ወይም በሌሎች ኮሚቴዎች ውስጥ ሊመረጥ ይችልል፡፡

በማናቸዉም ሁኔታ ቀደም ሲል በምግባረ-ብልሹነት ወይም እምነት በማጉደል የማይታወቅ፣ ያልተፈረደበት፣

¾ማህበሩ ከሚያከናውናቸው ሥራዎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በጥቅም የሚጋጭ ወይም ውድድር በሚያስከትል ተግባር ያልተሠማራ፣

በሌላ ሕዝባዊ ወይም መንግሥታዊ መዋቅር ተደራራቢ የሥራ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑ በጠቅላላ ጉባዔ የታመነበት፣

በተቻለ መጠን ማንበብና መፃፍ የሚችል

## የኅብረት ሥራ ማኅበር ስም፣

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር መጠሪያ ስም ይኖረዋል፤ የስም አወጣጡም ምክንያታዊ፣ ሕግንና የሕዝብን ሞራል የማይቃረን መሆን አለበት፡፡

2) ከማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ስም መጨረሻ “ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማህበር” የሚል ሐረግ መጻፍ ይኖርባቸዋል፡፡

3) አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት ስም፣ መለያ ምልክት እና የሥራ ክልል ውስጥ ሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር ተመሳሳይ እና አሳሳች ስም ወይም መለያ ምልክት መጠቀም አይችልም፡፡

4) የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ስም ጉልህ ሆኖ ተጽፎ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ሥራ በሚካሄድበት በማንኛውም ሥፍራ መለጠፍ አለበት፡፡ እንዲሁም በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤዎች፣ ሌሎች መግለጫዎችና በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስም በሚፈረሙ ሰነዶች ላይ መጻፍ ወይም ማኅተም መደረግ አለበት፡፡

5) ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፍቃድ ሳያገኝ “የኅብረት ሥራ ማህበር” የሚለውን ስያሜ መጠቀም አይችልም፡፡

## ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበር ምዝገባ

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን መመዝገብ አለበት፡፡

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለመመዝገብ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ጋር አያይዞ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል፤

ሀ) የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፤

ለ) መተዳደሪያ ደንብ ሦስት ቅጂዎች፤

ሐ) የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ስም፣ አድራሻና ፊርማ፤

መ) የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ስም፣ አድራሻና ፊርማ፤

ሠ) አባላት ሆነው የሚመዘገቡት ግለሰቦች አባል ለመሆን ብቁ መሆናቸውን የሚያስረዱ ዝርዝር መግለጫዎች

ረ) ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆን የአባል ኅብረት ሥራ ማህበራትን አድራሻ እና የተወካዮች ፊርማ፤

ሰ) ከሦስት እስከ አምስት ዓመት የሚደረስ የሥራ ዕቅድ፤ ሰነድ፤

ሸ) የመነሻ ካፒታሉን መጠንና ተሰብስቦ በባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን ወይም ባንክ በሌለበት አካባቢ ከሆነ መዝጋቢው በወሰነው የፋይናንስ ተቋማት መቀመጡን የሚያረጋግጥ ;

ቀ) የሚሠራበት ቦታ መግለጫ፤

በ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች መግለጫዎች፡፡

3) አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ መርምሮ የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ በዚህም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ በኅብረት ሥራ ማህበርነት የተመዘገበበት ቀን ይጠቀሳል፡፡

4) አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹን ኅብረት ሥራ ማህበር መመዝገብ አይገባውም ሲል የወሰነ እንደሆነ ምክንያቱን በጽሑፍ በማድረግ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ወኪሎች ከአመለከቱበት ቀን ጀምሮ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መግለፅ አለበት፡፡

5) የአመልካች ወኪሎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በጽሁፍ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸው ከሆነ፣ በክልል ሲሆን አግባብ ላለው የክልል ፍርድ ቤት ወይም በፌዴራል ደረጃ ሲሆን ለፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት በ8 ተከታታይ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ኅብረት ሥራ ማኅበሩ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የተመዘገበ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡

7) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር በተመዘገበበት ዓላማና በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ለተፈቀደለት የሥራ መስክ ሌላ ተጨማሪ የንግድ ፈቃድ ሳያስፈልገው ይሠራል፡፡

8) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) እስከ (ሸ) የተዘረዘሩት መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረጋግጥ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ የሚያገለግል ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት ሰጥቶ የተቀሩት መስፈርቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲሟሉ ማስደረግ ይችላል፡፡

9) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተቋቋመበት ዓላማና መርህ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ በዚህ ሕግ የተፈቀደለትን ሥራ እንዳይሠራ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሊያግድ ይችላል ፡፡

10) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) መሠረት የታገደው ኅብረት ሥራ ማህበር እግዱ እንዲነሳለት በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ካላመለከተ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሕጋዊ የማፍረስ እርምጃ ይወስዳል፡፡

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ (10) መሠረት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በሕግ የሰውነት መብት ይኖረዋል፡፡

2) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ ነው፡፡

**. የኅብረት ሥራ ማኅበር መተዳዳሪያ ደንብ**

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፤ መተዳደሪያ ደንቡ ይዘት የሚከተሉትን ይጨምራል፤

2) የኅብረት ሥራ ማኅበር መተዳዳሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሣኔ ሊሻሻል ይችላል፤ ሆኖም የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር መተዳዳሪያ ደንብ ማሻሻያ ሊጸና የሚችለው አግባብ ባለው ባለሥልጣን ቀርቦ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ይሆናል፡፡

## 6. የኅብረት ሥራ ማኅበር መተዳዳሪያ ደንብ

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፤ መተዳደሪያ ደንቡ ይዘት የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ስምና አድራሻ፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ዓላማና ተግባር፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የሥራ ቦታ እና አካባቢ፤

መ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎችን፤

ሠ) ስለኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባላት መብትና ግዴታዎች፤

ረ) ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ አመራር አካላት ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ተግባር፤

ሰ) አባላት ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስለሚወጡበትና ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ፤

ሸ) ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ አባላትና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ምርጫ፣ ሹመትና የሥራ ጊዜ እንዲሁም ከኃላፊነት ስለሚታገዱበት ወይም ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ፤

ቀ) ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስብሰባ አጠራር እና ስለድምጽ አሰጣጥ፤

በ) ስለትርፍ አመዳደብና ክፍፍል፤

ተ) ስለ ሂሣብ ምርመራ፤

ቸ) ስለ ሠራተኛ አቀጣጠር፤

ነ) ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጣ ደንብ እና መመሪያን የማይቃረኑ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

## 7. የኅብረት ሥራ ማህበራት ግዴታ

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት አባሎቻቸው የሚፈልጉትን አገልግሎት በተያዘው ዕቅድ መሠረት የማቅረብ፤

2) በአገሪቱ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ለቀጠሯቸው ሠራተኞች መብታቸውን የመጠበቅ፤

3) ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚያገኙት ገቢ ላይ ከገቢ ግብር በስተቀር ሌሎች ለመንግስት መከፈል የሚገባቸውን ክፍያዎች በሕጉ መሠረት ወቅቱን ጠብቆ ገቢ የማድረግ፤

4) የመተዳደሪያ ደንቡን አክብሮ የመስራት፤

5) ለሚመለከተው አካል አስፈላጊውን መረጃ በተጠየቀ ጊዜ የመስጠት፤

6) የተቋቋመበትን መርህ እና ዓላማ አክብሮ የመሥራት፣

### ሥራ ስለ መጀመር

1/ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ በዕቅዱ መሠረት ሥራ ካልጀመረ በተጨማሪ በሦስት ወር ውስጥ እንዲጀምር ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

2/ የኅብረት ሥራ ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ሥራ ካልጀመረ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሣብ ከተጣራ እና መፍረሱ ከተወሰነ በኋላ ምዝገባው ተሰርዞ ሕጋዊ ሰውነቱን እንዲያጣ ይደረጋል፡፡

### የምዝገባ ምስክር ወረቀትን ስለማሳደስ

1/ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በዚህ አዋጅ ተቋቁሞ ከተመዘገበ እና ሕጋዊ ሰውነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ መሠረት በየሦስት ዓመቱ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ማሳደስ አለበት፡፡

2/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላሳደሰ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## 8. የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባራትና ኃላፊነቶች፣

1) የኅብረት ሥራ ማኅበራት በየደረጃቸው በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ (9) የተመለከቱት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡፡

2) መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በዋናነት ግለሰብ አባላት በተናጠል መወጣት የማይችሉትንና ከአቅማቸዉ በላይ የሆነን የጋራ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግር መፍታት የሚችሉ ተግባራትን የሚያከናውኑ ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ) ለአካባቢው ህብረተሰብ ስለኅብረት ሥራ ማኅበር ፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ቅስቀሳ ማድረግ፤

ለ) የአካባቢ ልማት እና ጥበቃ ሥራ ላይ መሳተፍ፤

ለአባላት በቅድመ ምርት እና በድህረ ምርት ላይ ስለምርት ጥራት ሥልጠና መስጠት፤

መ) ለአባላት የመጋዘን አገልግሎት መስጠት፤

ሠ) የአባላትን ችግር የሚፈቱ ፕሮጀክቶችን የመንደፍ፤

ረ) የአባላትን ምርት በመረከብ ዕሴት በመጨመር አባል ለሆኑባቸው ዩኒዬን ወይም ፌዴሬሽን ማስረከብ ወይም የተሻለ የገበያ መዳረሻ በማፈላለግ መሸጥ፤

ሰ) ሌሎች በመተዳደሪያ ደንባቸው የተዘረዘሩ ተግባራትን የማከናወን፤

3/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች በዋናነት አባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በተናጠል መወጣት የማይችሉትን የጋራ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች መፍታት የሚችሉ ተግባራትን የሚያከናውኑ ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ) ለአባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በተሰማሩበት መስክ ሥልጠና መስጠት፤

ለ) ለአባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የማማከር አገልግሎት መስጠት፤

ሐ) ለአባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ መረጃ አገልግሎት መስጠት፤

መ) ለአባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የገበያ ትስስር ማመቻቸት፤

ሠ) የመጋዘን አገልግሎት መስጠት፤

ረ) የምርት ማሳደጊያዎችን እና የፍጆታ እቃዎችን በጅምላ ማቅረብ፤

ሰ)በአባላት ምርት ላይ እሴት መጨመር እና ሌሎች በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ማከናወን፡፡

## 9. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች

1) የኅብረት ሥራ ማኅበር ምርት የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ወይም ምርት የማምረት እና አገልግሎት የመስጠት ሁለገብ ተግባር አጣምሮ የሚያከናውን ሆኖ ሊመሠረት ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የሚደራጁት የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች በሕግ በተከለከሉ፣ የህዝብ ሞራላዊ ዕሴቶች በሚነኩ፣ የአካባቢን ደህንነት በሚጎዱ ተግባራት መደራጀት የማይቻል ሲሆን አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኢኮኖሚ አዋጭነትን እንዲሁም በሚደራጁበት አካባቢ ሀብት መኖሩን በጥናት በመለየት የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸውን የአማራጭ አይነቶች በማቅረብ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

### መነሻ ካፒታል

1) ማንኛውም መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር በሚያቀርበው የሥራ ዕቅድ እና የአዋጭነት ጥናት መሠረት ቢያንስ የመጀመሪያ ዓመት የሥራ ማስኬጃ ወጪዎቹን መሸፈን የሚያስችል ካፒታል ይዞ መመሥረት አለበት፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዩኒዬን ሊመሠረት የሚችለው በተደረገው የአዋጭነት ጥናት መሠረት ዕቅዳቸውን ለመፈፀም እንዲያስችል በጠቅላለላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሰረት አባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ቢያንስ የጠቅላላ ካፒታላቸውን 25% ያህል ዕጣ መግዛት ሲችሉ ነው፡፡

3) የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፌዴሬሽን ሊመሠረት የሚችለው በተደረገው የአዋጭነት ጥናት መሠረት ዕቅዳቸውን ለመፈፀም እንዲያስችል በጠቅላለላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሰረት አባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኔኖች ቢያንስ የጠቅላላ ካፒታላቸውን 30% ያህል ዕጣ መግዛት ሲችሉ ነው፡፡

### ከአባላት ዉጭ ለሌሎች አገልግሎት ስለመስጠት

1) የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከአባላት ዉጭ የሚሰጡት አገልግሎት በሚመሠረተው ውል መሠረት ሆኖ ለሚከተሉት ዓላማዎች ይሆናል፤

ሀ) መንግስት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በብድር ከመንግስት ካዝና ወጪ ተደርጎ የሚቀርቡ ግብዓቶችን ለማሰራጨት፤

ለ) ፍላጎትና አቅርቦትን ለማመጣጠን በመንግስት በኩል የሚቀርቡ የፍጆታ ዕቃዎችን ለማሰራጨት፤

ሐ) ከልዩ ልዩ ድጋፍ ሰጪ አካላት ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ ተዘዋዋሪ ብድሮች እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ለማሰራጨት፤ እና

መ) በእርሻ ሥራ ላይ ለተሰማሩ አርሶ አደሮች የምርት ማሳደጊያ ግብአቶችን ማቅረብ እና ምርታቸውን ለመረከብ፤

1) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዝርዝር አፈጻጸም በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 10. የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ለመሆን መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተመለከቱትን የሚያሟላ ማንኛውም ሰው የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ለመሆን ይችላል፡፡

2) አባልነቱ ለመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ከሆነ፣

ሀ) ዕድሜው 18 ዓመት የሞላው፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ዕጣ ለመግዛትና የመመዝገቢያ ክፍያ ለመክፈል የሚችል፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ዓላማና መተዳዳሪያ ደንብ የተቀበለና ግዴታዎችን ለመፈጸም ፈቃደኛ የሆነ፤

መ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡት ደንቦችና መመሪያዎች የተወሰኑ ሁኔታዎችን የሚያሟላ፡፡

3) አባልነቱ ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር በላይ ለሆነ ኅብረት ሥራ ማኅበር ከሆነ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ ኅብረት ሥራ ማኅበር መሆን አለበት፡፡

**<u>የአባላት መዝገብ ስለ ማደራጀት</u>**

1/ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር የአባላት መዝገብ ማደራጀትና መያዝ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተደራጀ የአባላት መዝገብ የሚከተሉትን ዝርዝር ይይዛል፤

ሀ) የመሠታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ከሆነ የእያንዳንዱን አባል ስም፣ አድራሻ፣ሥራ፣ዕድሜ እና ጾታ የያዘ ሲሆን ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ ስም፣አድራሻ፣የተመሰረተበት ዓመተ ምሕረት እና የተሰማራበት የሥራ መስክ ይሆናል፡፤

ለ) አባል የሆነበት ወይም አባልነቱን ያቋረጠበት ቀን፤

ሐ) እያንዳንዱ አባል የያዘውን የዕጣ መጠን እና የከፈለውን የመመዝገቢያ ክፍያ፤

መ) በመተዳደያ ደንቡ የተወሰኑ ሌሎች ዝርዝሮች፣

## <u>ልዩ ልዩ መዛግብትና ሰነዶች፣</u>

የአባላት መዝገብ

የአባላት የግል ፋይል

የቃለ ጉባዔ መዛግብት

የንብረት መዝገብ

የብድር መዝገብ

የአባላት የግል የሂሳብ ደብተር

የአባላት የግል የሂሣብ ቋት

የገቢ ደረሰኝ

የወጪ ማዘዣ

የገቢና የወጪ መዝገብ

አጠቃላይ የሂሳብ ቋት  እና ሌሎች ከሂሳብ አያያዝ መመሪያው የተመለከቱ የሂሳብ ቅጻ ቅጾችን ይጨምራል፡፡

የገንዘብ ቁጠባ ኅብረተሰቡ ከሚያገኘው ገቢ ላይ የተወሰነ ገንዘብ በመቆጠብ እራሱን በራሱ እንዲረዳና የቁጠባን ባህል እንዲያዳብር እንዲሁም በቁጠባ የተገኘውን ገንዘብ የብድር አገልግሎት በመስጠት ኅብረተሰቡን የሚያገለግል የገንዘብ ተቋም ነው፡፡

የገንዘብ ቁጠባ የሚሰጡት አገልግሎት ጉልህ በመሆኑ በሀገር፣ በአህጉር እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ማህበራቱ በይበልጥ እየተስፋፉ ይገኛሉ፡፡

# 12. የገንዘብ ቁጠባ አስፈላጊነት

የገንዘብ ቁጠባ ማለት በአንድ በተወሰነ የሥራ ክልል የሚኖሩ ወይም የሚሰሩ ግለሰቦች ተመሳሳይ ፍላጐትንና ፈቃደኝነትን መሠረት በማድረግ በድካማቸው ከሚገኝ ገቢ በየጊዜው ለመቆጠብና ኑሮን ለማሻሻልም ሆነ ለችግር ጊዜ ገንዘብ ሲያስፈልጋቸው ብድር ለማግኘት፣ የገንዘብ አጠቃቀምን ሥርዓት ለመልመድና ባንክ ነክ አገልግሎቶችን በአቅራቢያው ለማግኘት እንዲቻል ለማኅበሩ የሚያስፈልገውን ካፒታል ከአባላት በማሰባሰብ የሚቋቋምና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አባላት በባለቤትነት ይዘው የሚመሩት፤ የሚያስተዳድሩት፤ የሚቆጣጠሩት፤ የገንዘብ ተቋም ነው፡፡

አባላትና ኅብረተሰቡ የሚያገኙትን ገቢ በሥርዓት እንዲጠቀሙ ትምህርት ለመስጠት በግለሰቦች እጅ ተበታትኖ የሚገኘውንና በሥራ ላይ ያልዋለውን ገንዘብ በቁጠባ ለማሰባሰብ፣

አባላት ችግር ሲገጥማቸውም ሆነ ኑሮአቸውን ለማሻሻል ወይም ለሚኖራቸው ዕቅድ ማስፈጸሚያ ገንዘብ ሲያስፈልጋቸው ያለውጣ ውረድ ብድር ለማግኘት፣

ማህበራዊ ኑሮን በማጠናከር በአባላት መካከል እርስ በርስ የመረዳዳትና የመተሳሰብ  ልምድ እንዲያድግ ለማስቻል፣

ለሚፈጠሩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መፍትሔ ለመንደፍ እንዲሁም የአገሪቱን ማዕከላዊ የገንዘብ ክምችት እንዲዳብር የሚረዳ አስፈላጊ ህዝባዊ ባንክ ነው፡፡

## 12.1 የገንዘብ ቁጠባ ዓላማ

ሀ. አባላትና ብሎም ኅብረተሰቡ የሚያገኙት ገቢ በስርዓት እንዲጠቀሙበት ትምህርት  መስጠት፣

ለ.  አባላት በማኅበራቸው ገንዘብ እንዲቆጥቡ በማድረግ ኑሮአቸውን ማሻሻል፣

ሐ. ለአባላት ፈጣንና ምቹ በሆነ መንገድ በተገቢው ወለድ የብድር አገልግሎት በመስጠት ኅብረተሰቡን ኋላቀር ከሆኑና ለብዝበዛ ከሚያጋልጡ አራጣና ሌሎች የብድር ልምዶች ማላቀቅ፣

መ. ዘላቂነት ያለው የገንዘብ ተቋም በመፍጠር ሌሎች ባንክ ነክ አገልግሎት መስጠት፣

ሠ. በግለሰቦች እጅ ተበታትኖ የሚገኘውና በሥራ ላይ ያልዋለውን ገንዘብ በቁጠባ በማሰባሰብ የአገሪቱን ማዕከላዊ የገንዘብ ክምችት ማዳበር፣

## 12.2 የገንዘብ ቁ/ ተግባር፣

ሀ. የመመዝገቢያ ክፍያ፣ የዕጣ ክፍያ፣ መደበኛ ቁጠባ፣ መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ፣ የአገልግሎት ክፍያዎችንና ሌሎች ገቢዎችን ከአባላት መሰብሰብ፣

ለ. በየጊዜው እንደአስፈላጊነቱ ዕጣ አዘጋጅቶ መሸጥ፣

ሐ. የኅብረት ሥራ አዋጆችን፣ ይህን የአደረጃጀት መመሪያና ደንቦችን መሰረት በማድረግ ልዩ ልዩ የአፈፃፀም ደንብና መመሪያዎችን ማውጣት፣

መ. በብድር መመሪያው መሠረት የብድር አገልግሎት መስጠት፣ ተበዳሪ አባላት ገንዘባቸውን በአግባቡ መጠቀም ይችሉ ዘንድ ተገቢውን ምክር፣ዕገዛ፣ ክትትል፣ ትምህርት መስጠት፣ ለብድር የተሰጠው ገንዘብ በወቅቱ ከነወለዱ እንዲመለስ አስፈላጊውን መፈጸም፣

ሠ. በቁጠባ ሂሳብ ለተቀመጠ ገንዘብ ተገቢውን ወለድ ማሰብ፣

ረ. ለማህበሩ ጥቅም በሚያስገኝ ቦታ ገንዘብ ማስቀመጥ፣

ሰ. መደበኛ ያልሆነ ቁጠባውን ግለሰቦች ወጪ ለማድረግ በጠየቁ ጊዜ ማስተናገድ፣

ሸ. ተከታታይ ትምህርት፣ መረጃና ሥልጠና ለአባላት፣ ለአመራር አካላት፣ ለቅጥር ሰራተኞች እና አባል ለሚሆኑ ግለሰቦች መስጠት፣

ቀ. ለስራው የሚያስፈልጉትን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን ማፍራትና ማስተዳደር፣

## 12.3 መደበኛ ቁጠባ፣

መደበኛ ቁጠባ ማለት የገንዘብ ቁጠባ አባላት በሚወስኑት የቁጠባ ጊዜ እና የቁጠባ መጠን መሠረት ያለማቋረጥ የሚቆጥቡት የቁጠባ ዓይነት ሲሆን፣ አባላት ከማኅበሩ በተለያየ ምክንያት አባልነታቸውን እስካላቋረጡ እንዲሁም የአንድ አባል የተጠራቀመ ቁጠባ መጠን በገጠር ከብር 50,000/ ሃምሳ ሽህ/ና በከተማ ከብር 100,000/አንድ መቶ ሽህ/ በታች ከሆነ ወጪ ሆኖ አይሰጥም፡፡ አባላት የመደበኛ ቁጠባ ክፍያ ጊዜውን በግልጽ በመተዳደሪያ ደንባቸው ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የገቢ መጠንን፣ ፍላጎትን፣ ዕቅድን የቤተሰብ ብዛትን እንዲሁም የኑሮ ደረጃን መሠረት አድርጐ ለዕቅድ ዝግጅት፣ ለአሰራር፣ ለክትትል እንዲያመች ጠቅላላ ጉባዔው ዝቅተኛውን የመደበኛ ቁጠባ በመተዳደሪያ ደንቡ ይወስናል፡፡

አባላት የመቆጠብ አቅማቸውን መሠረት አድርገው ከላይ በተቀመጠው የቁጠባ መጠን ገደብ ውስጥ ያለማቋረጥ በቁጠባ ጊዜው ሊቆጥቡ የወሰኑትን የገንዘብ መጠን በማመልከቻ ይገልፃሉ፡፡ አባላት ገደቡን ጠብቀው የመደበኛ ቁጠባ መጠናቸውን ከፍ ወይም ዝቅ ማድረግ ይችላሉ፡፡ የቁጠባ መጠናቸውን ማሣደግ ወይም መቀነስ ሲፈልጉ ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው በየስድስት ወሩ በጥርና በሐምሌ ወር ነው፡፡

## 12.4 መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ፣

መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ ማለት የገንዘብ ቁጠባ አባል የሆኑና ያልሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚቆጥቡትና በፈለጉ ጊዜ ወጭ አድርገው የሚጠቀሙበት የቁጠባ አይነት ነው፡፡

ከማኅበሩ አባላት ውስጥ ተከታታይ ገቢ የሌላቸው አባላት በአንድ ወቅት ሊያገኙ የሚችሉትን የገንዘብ መጠን መደበኛ ባልሆነ ቁጠባ ውስጥ አስቀምጠው ቀደም ብለው በመደበኛ ቁጠባ ለመቆጠብ በወሰኑት የገንዘብ መጠን መሠረት ከመደበኛ ያልሆነ ቁጠባ ተቀናሽ እየሆነ ወደ መደበኛ ቁጠባ እየተዛወረ እንዲቆጠብ የማድረግ አማራጭ ይኖራል፡፡

መደበኛ ካልሆነ ቁጠባ የሚሰበሰብ ገንዘብ በጥናት ላይ ተመስርቶ በጥንቃቄ ለብድር አገልግሎት ሊውል ይችላል፡፡

መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ የሚያስገኘው ጥቅም ወለድ ብቻ በመሆኑ በከተማም ሆነ በገጠር የሚቋቋመው ወይም የተቋቋመው የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበሩ መደበኛ ያልሆነ ቁጠባን ለማበረታታት የሚከፈለውን የወለድ መጠን በአካባቢው ያሉ የፋይናንስ ተቋማት ከሚከፍሉት የወለድ መጠን ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል፡፡ መጠኑም በጠቅላላ ጉባዔው እንዲወሰን ይደረጋል፡፡ መደበኛ ላልሆነ ቁጠባ የሚከፈለው የወለድ መጠንም ለሚቆጥቡ ሰዎች በቅድሚያ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

መደበኛ ላልሆነ ቁጠባ የሚከፈለው የቁጠባ ወለድ መጠንና የመክፈያ ጊዜ ከመደበኛ ቁጠባ የመክፈያ ጊዜ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

## ስጦታ፣ እርዳታ፣ሽልማት

ማኅበሩ ከግለሰቦች ከድርጅቶች ከመንግስት በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ስጦታ፣ እርዳታ፣ሽልማት ሊያገኝ ይችላል፡፡ ይህም የማኅበሩ የጋራ ሀብት ይሆናል፡፡ ማኅበሩ እንኳ ቢፈርስ በስጦታ፣ በእርዳታና በሽልማት የተገኘው ሀብት ለሌላ ተመሳሳይ የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት በህጋዊ መንገድ የሚመጡ ተዘዋዋሪና ሌሎች የፕሮጀክት ብድሮችን በማኅበሩና በፕሮጀክቶች መካከል በሚደረግ ስምምነት ተረክቦ ማስተዳደር ይችላሉ፤